*መመሪያ ቁጥር ……/***2015**

ኢትዮጵያ እና ጂቡቲ የተፈራረሙትን የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ

ኢትዮጵያ እና ጂቡቲ በሚዋሰኑባቸው የድንበር አካባቢዎች የሚገኙ የሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች ከመሀል ሀገር በቀላሉ ሊያገኟቸው የማይችሏቸውን መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች በጠረፍ ንግድ እንዲቀርቡላቸው ለማድረግ የሚያስችል የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ. ፌብሯዋሪ 7 ቀን 2015 ዓ.ም ጂቡቲ ላይ የተፈራረሙ በመሆኑ፤

በጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮሉ አንቀጽ 6 ተፈራራሚ ሀገራቱ የጠረፍ ንግድ ማስፈጸሚያ መመሪያ በማውጣት ፕሮቶኮሉን መተግበር እንዳለባቸው የተመለከተ በመሆኑ፤

በድንበር አካባቢ ህጋዊ የጠረፍ ንግድ ስርዓትን በመዘርጋት በአካባቢው የሚስተዋለውን የኮንትሮባንድ እና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ መቀነስ እና በኢትዮጵያ እና በጂቡቲ ጎረቤት ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር በድንበር አካባቢ ሰላምና ፀጥታ ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 52(2) እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ ቁጥር 392/2009 አንቀጽ 53 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል **1**

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ እና የጂቡቲ የጠረፍ ንግድ መመሪያ ቁጥር___2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"**የድንበር አካባቢ" ማለት በዚህ መመሪያ አባሪ 3 የተዘረዘሩት የጠረፍ ንግድ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ናቸው፤
2) **"**የጠረፍ ንግድ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የጠረፍ ንግድ ፈቃድ በተሰጣቸው ነጋዴዎች በድንበር አካባቢ የሚካሄድ የንግድ እንቅስቃሴ ነው፤
3) **"**የጠረፍ ንግድ ፈቃድ" ማለት የጠረፍ ንግድ ለማካሄድ የሚያስችል በድንበር አካባቢ ለሚኖር የተፈጥሮ ሰው የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ነው፤
4) **"**የጠረፍ ነጋዴ" ማለት ሕጋዊ የጠረፍ ንግድ ፈቃድ የተሰጠው በሌላ መደበኛ የንግድ ሥራ ያልተሰማራ በድንበር አካባቢ የሚኖር የተፈጥሮ ሰው ነው፤

5) **“**የጠረፍ ንግድ ምርቶች” ማለት በዚህ መመሪያ በአባሪ-1 እና በአባሪ-2 የተዘረዘሩት የወጪ ምርቶች እና የገቢ ምርቶች ናቸው፤

6) **“**የድንበር በር” ማለት ኢትዮጵያ ከጂቡቲ ጋር በምትዋሰንበት ድንበር የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አገልግሎት የሚሰጥባቸው የመውጫና መግቢያ በሮች ናቸው፤

7) **“**ሚኒስቴር” ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

8) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u> ፡-

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ እና በጂቡቲ መካከል በሚካሄድ የጠረፍ ንግድ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ።

ክፍል ሁለት

ስለ ጠረፍ ንግድ

4. <u>የጠረፍ ንግድ ምርቶች</u>

1/ የጠረፍ ነጋዴ ከኢትዮጵያ ወደ ጂቡቲ ማስወጣት የሚችለው በዚህ መመሪያ አባሪ-1 የተዘረዘሩትን የወጪ ምርቶች ብቻ ነው።

2/ የጠረፍ ነጋዴ ከጂቡቲ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት የሚችለው በዚህ መመሪያ አባሪ-2 የተዘረዘሩትን የገቢ ምርቶች ብቻ ነው።

3/ የጠረፍ ነጋዴ በወር የሚያስገባው እና የሚያስወጣው የምርት መጠን ግምት ከ 1000 የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር ወይም ተመጣጣኝ የጂቡቲ ፍራንክ መብለጥ የለበትም።

4/ የጠረፍ ነጋዴ የሚነግደው ምርት መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተጠቀሰው ግምት እስካልበለጠ ድረስ በወር ሁለት ጉዞዎችን ሊያደርግ ይችላል።

5/ የጠረፍ ነጋዴ የሚነግደውን የምርት ዓይነት፣ መጠን እና ብዛት በመውጫና መግቢያ የድንበር በር የጉምሩክ ኮሚሽን ሰራተኞች በሚያቀርቡለት ዴክላራሲዮን ላይ መሙላት፣ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማቅረብ እና ክፍያዎች መፈጸም አለበት።

5. <u>የወጪና የገቢ ምርቶች ዋጋ</u>

1/ የወጪ ምርቶች የመሸጫ የዋጋ ግምት የሚሰላው ሚኒስቴሩ ወይም እርሱ የሚወክለው የክልል መስተዳድር በሚያወጡት ወቅታዊ የምርቶች የዋጋ ዝርዝር መሰረት ይሆናል።

2/ የገቢ ምርቶች ዋጋ በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሚወሰን ይሆናል።

6. <u>የድንበር በር አገልግሎቶች</u>

በድንበር በር የጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡-

1/ የጠረፍ ነጋዴዎች የሚያስወጡትንና የሚያስገቡትን ምርቶች ዓይነት፣ ብዛት እና መጠን እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የሚሞሉበት ዴክላራሲዮን የማቅረብና የማስሞላት፤

2/ የጠረፍ ነጋዴ ከኢትዮጵያ ወደ ጂቡቲ ለማስወጣት በዴክላራሲዮን ላይ የሞላው የምርት ዓይነት፣ ብዛት እና መጠን ትክክል መሆኑን፣ ነጋዴው በወር ያስወጣው ምርት ጠቅላላ መጠን ከ1000/አንድ ሺህ/ የአሜሪካን ዶላር/ ወይም ተመጣጣኝ ኢትዮጵያ ብር/ አለመብለጡን እንዲሁም ምርቶቹ በዚህ መመሪያ አባሪ-1 የተዘረዘሩት መሆናቸውን በማረጋገጥ ምርቱ እንዲወጣ የመፍቀድ፤

3/ የጠረፍ ነጋዴው ከጂቡቲ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት በዴክላራሲዮን ላይ የሞላው ምርት ዓይነት፣ ብዛት እና መጠን ትክክል መሆኑን፤ ነጋዴው በወር ያስገባው ምርት ጠቅላላ መጠን ከ1000/አንድ ሺህ/ የአሜሪካን ዶላር/ ወይም ተመጣጣኝ ኢትዮጵያ ብር/ አለመብለጡን እንዲሁም ምርቶቹ በዚህ መመሪያ አባሪ-2 የተዘረዘሩት መሆናቸውን በማረጋገጥ አስፈላጊ ክፍያዎችን በማስከፈል ምርቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የመፍቀድ፤

4/ አንድ የጠረፍ ነጋዴ በአንድ ጉዞ ይዞ በወጣው የወጪ ምርት መጠን ልክ ወደ አገር ውስጥ ማስገባቱን የማረጋገጥ፤

5/ ማንኛውም የጠረፍ ነጋዴ ምርት ይዞ ወደ ጂቡቲ በሚወጣበት ጊዜ የጠረፍ ንግድ ፈቃዱን የመያዝ እና ነጋዴው ሲመለስም ግዴታውን መወጣቱን በማረጋገጥ ፈቃዱን የመመለስ፤

6/ የጠረፍ ንግድ ፈቃዱን አስይዞ የወጣ ነጋዴ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ግዴታውን አሟልቶ ፈቃዱን ካልወሰደ ፈቃዱን ለሚኒስቴሩ የማስረከብ።

7. <u>የጠረፍ ንግድ መውጫና መግቢያ በሮች</u>

የጠረፍ ነጋዴዎች የጠረፍ ንግድ ምርቶችን ማስወጣትና ማስገባት የሚችሉት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አገልግሎት በሚሰጥባቸው የድንበር በሮች በኩል ነው።

8. <u>የመረጃ ልውውጥ እና ሪፖርት አቀራረብ</u>

1/ ሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ ውክልና የተሰጠው የክልል መስተዳድር በአባሪ-1 የተዘረዘሩትን ወጪ ምርቶች ወቅታዊ የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር ለድንበር በር የጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ያሳውቃል።

2/ ሚኒስቴሩ የሰጠውን/ያደሰውን የንግድ ፈቃድ መረጃ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ያሳውቃል።

3/ የድንበር በር የጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የወጪና ገቢ ዕቃዎች ስታትስቲካዊ ሪፖርት እያዘጋጀ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ያቀርባል፣ ኮሚሽኑም ይህንኑ ሪፖርት መርምሮ ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሪፖርት ያቀርባል።

ክፍል ሶስት

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

9. <u>የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

1/ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ የጠረፍ ንግድ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የንግድ ሥራ ፈቃድ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚከተሉት ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

(ሀ) የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (እንደተሻሻለው)፣ አንቀጽ 35፤

(ለ) የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ ቁጥር 392/2009 (እንደተሻሻለው) ከአንቀጽ 42 እስከ 47፤ እና

(ሐ) የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 935/2015 ከአንቀጽ 33 እስከ 38።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የተጠቀሱትን ሕጎች ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አያስቀርም።

10. <u>ውክልና የተከለከለ ስለመሆኑ</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት የጠረፍ ንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን በውክልና፣ በውሰት ወይም በሌላ መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም የሌላ ሰው የጠረፍ ንግድ ፈቃድን መጠቀም የተከለከለ ነው፤

11. <u>አባሪዎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙት አባሪ-1፣ አባሪ-2 እና አባሪ 3 የዚህ መመሪያ አካል ናቸው።

12. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ ___ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ

ገበረ መስቀል ጫላ ሞጣሎ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

አባሪ **1**፡ ከኢትዮጵያ ወደ ጀቡቲ የሚላኩ የጠረፍ ንግድ ምርቶዝ ዝርዝር

1. የቁም እንሰሳት (በሬ፣ ፍየል፣ በግ፣ እና ግመል)
2. የእንሰሳት ተዋጽኦ (ወተት፣ ቅቤ እና የተፈጥሮ ማር)
3. በአካባቢው የተመረቱ አትክልትና ፍራፍሬዎች
4. የተፈጨ ሹሮና በርበሬ
5. በአካባቢው የተመረቱ የእደ-ጥበብ ውጤቶች
6. ማሽላ እና
7. በቆሎ

አባሪ **2**፡ ከጀቡቲ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የጠረፍ ንግድ ምርቶዝ ዝርዝር

1. ፔርሙስ ብርጭቆዎችና ሳህኖች
2. የምግብ ዘይት/በጋሎን/
3. ፓስታ መኮረኒና ዱቄት
4. የዱቄት ወተት/Milk powder
5. ስኳር
6. ተምር
7. ሩዝ
8. ልዩ ልዩ ብረት ድስቶች
9. ሰንደልና ሌሎች የሚጨሱ
10. ክብሪት
11. አነስተና መጠን ያላቸው ከፕላስቲክና ከወፍራም ክር የተሰሩ የወለል ምንታፍና ማስጌጫዎች
12. ባትሪ ከነባትሪ ድንጋዩ
13. እጣን
14. ፋኖስ
15. ትንንሽ ምድጃዎች/Stove /small scale/
16. ሻማዎች
17. በድንበር አካባቢ በሚኖሩ ህዝቦች የሚጠቀሙባቸው አይነተኛ ልብሶችና ጫማዎች
18. ደብተር፣ እስክርቢቶና እርሳስ
19. የሻይ ቅጠል/ቅመም
20. እርሾ /Baking powder/

አባሪ **3**፡- የጠረፍ ንግድ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች

1. በኢትዮጵ በኩል የጠረፍ ንግድ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች

ዱብቲ፣ አፋምቦ፣ ኢይሳታ፣ ኢሊዳኢር፣ አፍዴራ፣ ቆሬ፣ ቢዲ ደንበል፣ ቢዩጉርጉር እና አይሻ ናቸው

2. በጂቡቲ በኩል በኩል የጠረፍ ንግድ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች

ከጋላፊ እስከ የቦኪ፣ ከጋሊሌ እስከ ኤልሳቤህ፣ ከባልሆ እስከ ዶራ፣ ከቦንዳራ እስከ ዲኪሂል ናቸው።